የኢትዮጵያ የንግድና ዘርፍ ማኅበራት ምክር ቤት የሳምንታዊ መረጃ ማሰራጫ

# ሳምንታዊ የቢዝነስ መረጃዎች

**በኮሙኒኬሽንና ህዝብ ግንኙነት መምሪያ የሚዘጋጅ**

ከታህሳስ 20 - 28፤ 2017 ዓ.ም
DEC 29- JAN 6, 2024 G.C

## 1.ገንዘብ ሚኒስቴር የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ አደረገ

**Reporter: January 5, 2025**

- የድንጋይ ከሰል ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ወደ አገር ውስጥ እንዲገባ የተላለፈው ውሳኔ ተሸሯል

አምራችና ገጣጣሚ ኢንዱስትሪዎች ይበልጥ ተወዳዳሪ ሆነው ገቢ ምርቶችን በአገር ውስጥ ለመተካት እንዲሁም ውጤታማ ለማድረግና የታሪፍ ከለላ እንዲኖራቸው በሚል፣ የገንዘብ ሚኒስቴር የጉምሩክ ታሪፍ ማሻሻያ ማድረጉ ታወቀ፡፡

ገንዘብ ሚኒስቴር ተግባራዊ እንዲደረግ በሚል ያዘዘው የጉምሩክ ቀረጥ ማስከፈያ ማሻሻያ ከታኅሳስ 23 ቀን 2017 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲደረግ የተወሰነ ሲሆን፣ ጉምሩክ ኮሚሽንም ለሁሉም የጉምሩክ ሥነ ሥርዓት ለሚፈፀምባቸው ቅርንጫፍ ጽሕፈት ቤቶች በጻፈው ደብዳቤ፣ በጉምሩክ ማሻሻያው መሠረት አገልግሎት እንዲሰጡ አሳስቧል፡፡

የታሪፍ ምጣኔያቸው ከተሻሻለ የዕቃ ዓይነት ውስጥ ለሞተር መኪናዎች/ለስቴሽን ዋገኖችና ለሽቅድድም መኪናዎች ጭምር የሚያገለግል 25 በመቶ የጉምሩክ ቀረጥ ልክ እንዲከፍል የተባለ ሲሆን፣ ለአውቶቢስ ወይም የጭነት መኪናዎች የሚያገለግሉ ዓይነት ዕቃዎች በተመሳሳይ ልክ የጉምሩክ መጠን የታሪፍ ምጣኔያቸው መሻሻሉ ታውቋል።

በሌላ በኩል በታሪፍ ቁጥር 8703 ውስጥ 2321 ላይ የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች 25 በመቶ የታሪፍ ምጣኔ እንዲሁም በተመሳሳይ 2322 የሚመደቡ ተሽከርካሪዎች 35 በመቶ የታሪፍ ምጣኔ እንዲኖራቸው ማሻሻያ ያደረገው የገንዘብ ሚኒስቴር፣ በቀጥታ ለምግብነት የሚውል ዘይት ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ ሆኖ እንዲገባ የተላለፈው ውሳኔ ተፈጻሚነት እስከቀጠለ ድረስ፣ በግብዓትነት የሚያገለግሉ በታሪፍ መጽሐፉ ምዕራፍ 15 ውስጥ የተዘረዘሩ ዘይቶች ከጉምሩክ ቀረጥ ነፃ እንዲሆኑ ተወስኗል።

https://www.ethiopianreporter.com/137095/

## 2. ልዩ የኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ለማግኘት መነሻ የፋይናንስ መጠን 75 ሚሊዮን ዶላር ማቅረብ ግዴታ የሚጥል ረቂቅ መመርያ ተዘጋጀ

**January 5, 2025**

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ እንዲሰጠው ጥያቄ ያቀረበ አልሚ አስተማማኝ የካፒታል ምንጭ ያለውን ለዞን መሠረተ ልማና ተያያዥ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ የሚመድበው፣ አነስተኛ የኢንቨስትመንት ፋይናንስ መጠን 75 ሚሊዮን ዶላር ግዴታ መሆን እንዳለበት የሚደነግግ ረቂቅ መመርያ ተዘጋጀ፡፡

በልዩ ኢኮኖሚ ዞን አዋጅ ቁጥር 1322/2016 ድንጋጌ መሠረት ‹‹የኢትዮጵያ ኢንቨስትመንት ቦርድ›› መመርያ እንዲያወጣ ሥልጣን ሰጥቶታል፡፡ በአዋጁ መሠረት የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ ማቋቋም ልማት አስተዳደር፣ ቁጥጥርና ተቋማዊ ግንባታ የሚመለከቱ ፖሊሲዎችንና ሕጎችን በተመለከተ፣ የስትራቴጂካዊ አመራርና ውሳኔዎች የቦርዱ ኃላፊነት እንደሆነ ተቀምጧል፡፡

በዚህ ረቂቅ መመርያ ክፍል ሦስት ላይ የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜን የሚመሩ ዝርዝር መመዘኛዎችን ያካተተ ሲሆን፣ በአንቀጽ 7 ደግሞ የአመልካች የኢንቨስትመንት ፋይናንስ አቅምና ምንጭ ምን ያህል መሆን እንዳለበት አስቀምጧል፡፡

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስያሜ እንዲሰጥ ጥያቄ ያቀረበ አልሚ ወይም ንዑስ አልሚ፣ አስተማማኝ የካፒታል ምንጭ ያለው መሆኑን የሚያሳይ ማስረጃ የማቅረብ ግዴታ እንዳለበት በአንቀጽ 7 (1) ላይ በረቂቅ መመርያው ተቀምጧል፡፡

በዚሁ አንቀጽ አልሚው ለዞኑ መሠረተ ልማትና ተያያዥ አገልግሎት መስጫ ተቋማት ግንባታ የሚመድበው አነስተኛ የኢንቨስትመንት መጠን፣ 75 ሚሊዮን ዶላርና ለንዑስ አልሚ ደግሞ 40 ሚሊዮን ዶላር መሆን እንዳለበት ያስቀምጣል፡፡

https://www.ethiopianreporter.com/137083/

## 3. በነዳጅ አቅርቦት ላይ ሰው ሰራሽ እጥረት እንዲፈጠር የሚያደርጉ ከምርት መሰወር ጋር በተያያዘ በሕግ ተጠያቂ ይሆናሉ - ባለስልጣኑ

**ኢ.ዜ.አ፡ ታህሳስ 27/2017**

በነዳጅ አቅርቦት ላይ ሰው ሰራሽ እጥረት በየጊዜው እንዲፈጠር የሚያደርጉ ከምርት መሰወር ጋር በተያያዘ በሕግ ተጠያቂ እንደሚሆኑ የነዳጅና ኢነርጂ ባለስልጣን አስታወቀ።

ነዳጅ ጭነው ያለአግባባ በየቦታው ቆመው የሚገኙ የነዳጅ ጭነት ተሽከርካሪዎች የአፋር ክልል ንግድ ቢሮ ባለስልጣን መስሪያ ቤቱ በጠየቀው ትብብር መሠረት ከክልሉ የፀጥታ አካል ጋር በመሆን በሰጠው ምላሽ ከተደበቁበት እንዲወጡ በማድረግ ላይ ይገኛል፡፡

በዚህም አዲስ አበባን ጨምሮ ለተለያዩ ክልሎች የሚጓጓዝን ነዳጅ ይዘው በአፋር ክልል ልዩ ቦታው ሰርዶ አድማስ በሚባል ቦታ በየጥሻው የቆሙ ቦቴዎች የፀጥታ አካል ባደረገው አሰሳ ተደብቀው በቆሙበት ተይዘዋል ብሏል፡፡

በወሩ መጨረሻ የነዳጅ ዋጋ ክለሳ ይሠራል በሚል ያልተጨበጠ ተስፋ ነዳጁን ይዘው የተሸሸጉት እነዚህ ተሽከርካሪዎች ያለአግባባ የሚያገኙትን ትርፍ ከማሰብ ውጪ የጫኑት ነዳጅ በባህሪው በትነት የሚባክን፣ አደጋን የማስከተል አቅም ያለው መሆኑን ለማሰብ አልፈቀዱም፡፡

በአንጻሩ ከዚህ ባለፈ በየክልል ከተሞች የነዳጅ ማደያዎችን በማድረቅ እጥረት በመፍጠር ህብረተሰቡን የማጉላላት ስራን መስራታቸውን ማመን አይፈልጉም ሲልም ገልጿል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5750181

## 4. በቡና ልማት ምርት እና ምርታማነት መጨመሩ፣ ጥራት እና የውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይ የታዩ መሻሻሎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው - ቋሚ ኮሚቴው

**ኢ.ዜ.አ፡ ታህሳስ 27/2017**

በቡና ልማት ምርት እና ምርታማነት መጨመሩ፣ በጥራት እና በውጭ ምንዛሬ ግኝት ላይ የታዩ መሻሻሎች ተጠናክረው መቀጠል እንዳለባቸው በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የግብርና ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ አስገነዘበ።

የኢትዮጵያ ቡናና ሻይ ባለስልጣን አመራሮች ለቋሚ ኮሚቴው ከቡና ምርት ትመና ጋር በተያያዘ ማብራሪያ በመስጠት በጉዳዩ ላይም ውይይት ተደርጓል።

በውይይቱ ማጠቃለያ ላይ የቋሚ ኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ሰለሞን ላሌ ምርት እና ምርታማነት መጨመሩ፣ በጥራት በኩል የታዩ መሻሻሎች እንዲሁም የውጭ ምንዛሬ ግኝት እድገቱ የሚደነቁ ውጤቶች በመሆናቸው ተጠናክረው መቀጠል ይኖርባቸዋል ብለዋል፡፡

የባለስልጣኑ ዋና ዳይሬክተር አዱኛ ደበላ በበኩላቸው መንግስት ለቡናው ዘርፍ ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የ2016/2017 የቡና ምርት ትመናን በተመለከተ የተካሄደውን ዳሰሳ በተመለከተም ለቋሚ ኮሚቴው ዝርዝር ማብራሪያ አቅርበዋል።

በዚህም የምርት ትመናው ሲካሄድ የምርምር ተቋማት፣ የባለስልጣኑ እንዲሁም ሌሎች በዘርፉ የካበተ እውቀት እና ልምድ ያላቸውን ባለሙያዎች በማሳተፍ መሳተፋቸውን ጠቁመዋል።

በመሆኑም ትመናው ሲካሄድ ተገቢውን ሳይንሳዊ ሂደት ተከትሎ፤ ዞን፣ ወረዳ እስከ አርሶ አደር ማሳ ድረስ በመውረድ ወካይ የሆኑ ናሙናዎች ተወስደው መሆኑን አስረድተዋል፡፡

ትንታኔውም የተለየ ጥንቃቄ ተደርጎ ሂደቱም ከስር ከስር ክትትል ከምርት ትመናው በተጨማሪ ከእያንዳንዶቹ ዝርያዎች አንጻር ምን ያህል ተመረቱ የትስ ላይ እንገኛለን? ከበሽታ መከላከል እና ቁጥጥር፣ ከደባል ሰብሎች፣ ከቡና እደሳና ጉንደላ፣ ኩትኳቶ፣ ኮምፖስት አጠቃቀም፣ የአርሶ አደሩ የተሟላ ፓኬጅ አጠቃቀም፣ እና ሌሎች ጉዳዮችን ያካተተ መሆኑን እና ሳተላይት ምስሎችን በመጠቀም ጭምር መከናወኑን አብራርተዋል፡፡

https://www.ena.et/web/amh/w/amh_5747002

**5. NBE pauses independent forex bureau licensing pending evaluation**

**The Reporter: January 4, 2025**

Regulators at the National Bank of Ethiopia (NBE) are no longer processing license requests for new applicants seeking to get involved in the forex trading business. In early October 2024, the central bank announced it had issued licenses to five independent foreign exchange bureaus in a bid to undercut the parallel market following the floating of the currency a few months prior.

Dugda Fidelity Investment PLC, Ethio Independent Foreign Exchange Bureau, Global Independent Foreign Exchange Bureau, Robust Independent Foreign Exchange Bureau, and Yoga Forex Bureau were the recipients.

Regulators are evaluating how the five firms are performing before proceeding to process applications for new licenses, according to Yenehassab Tadesse, director of forex monitoring and reserve management at NBE.

https://www.thereporterethiopia.com/43235/

**6. Ethio telecom CEO petitions Parliament for feasible land policies to back infrastructure expansion**

**The Reporter: January 4, 2025**

The chief executive of the state-owned Ethio telecom says unsuitable land acquisition procedures, particularly in the country's urban centers, are the primary obstacle to the operator's infrastructure expansion plans. CEO Frehiwot Tamiru addressed the comments to the parliamentary committee for Public Enterprises and Institutions Affairs this week, which conducted a review of Ethio telecom and the Ethiopian Telecommunications Authority this week. MPs criticized the operator for unreliable telecom services, the absence of telecom products and services in rural areas, and the unaffordability of its products.

Frehiwot outlined challenges hindering the state-owned enterprise, including land acquisition, security concerns, financial constraints, inaccessible roads, lack of commercial electricity, vandalism, and fraud. However, she emphasized difficulties in obtaining land and excessive compensation demands—especially in urban centers—as the most significant hurdles.

https://www.thereporterethiopia.com/43218/#google_vignette

**7.Ethiopia Expanding Power Export Network, Bolstering Regional Integration**

**ENA: January 3/2025**

Ethiopia is expanding its role as a regional energy powerhouse with electricity exports poised to significantly contribute to its economic growth and foster closer ties with neighboring nations.

Ethiopia, which is currently supplying power to Sudan, Kenya and Djibouti, is on the verge of commencing electricity export to Tanzania, a crucial step in its ambition to become a regional energy hub.

Ethiopian Electric Power CEO, Ashebir Balcha confirmed today that final grid testing for the Tanzania connection is underway.

Pointing out the growing regional demand for Ethiopia's reliable and competitively priced electricity, he said formal requests from countries like South Sudan have also been received.

https://www.ena.et/web/eng/w/eng_5738069

**8. Macroeconomic reform: A catalyst for sustainable development**

**Ethiopian Press: January 2, 2025**

The Ministry of Industry has recently stated that macroeconomic reforms implemented by the Ethiopian government since July have successfully addressed key bottlenecks in the manufacturing sector.

Industry State Minister, Hasan Muhumed Moalin, told ENA that the reforms have, for example, alleviated the long-standing foreign currency shortage that previously hindered manufacturers' ability to import essential inputs, spare parts, and machinery.

It should be recalled that the ministry recently organized a public-private dialogue aimed at addressing challenges and seizing opportunities to unlock the potential of the manufacturing sector.

"We had a public-private dialogue focused on our economy, led by the private sector, which plays a crucial role," Hasan said. "Therefore, it is important to understand the problems, challenges, and opportunities arising from the macroeconomic reforms. In this context, foreign exchange was a major constraint for the manufacturing sector, limiting the importation of spare parts, inputs, and machinery. However, the macroeconomic reform has completely resolved this issue."

To support manufacturers, the government has addressed foreign currency constraints, improved access to finance and electricity, and prioritized financial services for the manufacturing sector, said the State Minister.

The government has also included the manufacturing sector in its national development plan, alongside other key sectors, recognizing its crucial role in domestic consumption, export growth, import substitution, and overall economic development.

https://press.et/herald/?p=108499